ድንጉቴ ሪዝቅ

ብዙ የአላህ ሪዝቆች ሳናስባቸዉና ሳንጠብቃቸው የሚመጡ ድንጉቴ ናቸው:: ታዳያ ሪዝቅ ሲባል ገንዘብ ብቻ አይደለም:: ሥራ፣ ትዳር፣ ዛይኛ፣ ልጅ፣ የትምህርት ዕድል ... ሌላም ያጠቃልላል:: ሌላው በቀር በተሰበርከበት አጋጣሚ ቁና ሊያረግህ ድግሰት የመጣልህ የማጽናኛና የማስታወሻ ቃል ራሱ ሪዝቅ ነው። ድንጉቴ ሪዝቅ።

ወትዉተን ወትዉተን ... አንደው አላህዬ ብለን ዱዓ አድርገን የዱዓችን ምላሹ ሲዘገይ አላህ የረሳን ይመስለናል አይደል!:: እሱ ዝም ሲል ጉዳያችን ጉዳዩ እንዳልሆነ መሰሎን ሀሳብ ይገባናል አይደል ... ላ ላ ወላሂ:: ... እሱ የፈጠራቸዉን ባሮቹን ይረሳቸዋል ብሎ ከሚያስብ በላይ በዳይ ፍጡር የለም:: እንዲህ የሚያስብ ሰው ራሱንም አምላኩንም የበደለ ነው:: እኛ የአላህ ባሮች ነን፣ አላህ ባሮቹን ጥሎ አይጥልም:: እናም ዱዓችን አላህ ዘንድ ተቀምጧል ማለት ነው:: ዛሬ፣ ነገ ይሁን ወደፊት በምንጠብቀዉም ሆነ በሌላ መልኩ ምላሹን እንጠብቃለን:: እሱም የሆነ ቀን የሆነ ነገር ችሮን ያሰደነግጠናል:: ከአላህ በላይ የፈጠረዉን ፍጡር ሰዉን ሰርፕራይዝ ማን አለ በረቢ!:: ስለዚህ አላህ ባሮቹን ይወዳል ማለት ነው::

አመልከተህ በረሳኸው ሥራ ድንገት ተጠርተህ አታውቅም ወይ!? እንዴት መቼ አመለከትኩ አትበል፣ በአላህ ሱ.ወ. እጅ የተያዘ ጉዳይ ነበርና ባይሆን ዶሎ አቤት በል፡ : ሰው ተላላኪ ነው፣ አላህ ነው ኡድራጊ ፈጣሚው:: መልካም ትዳር ተመኝቼላቸው ግና ተሰፋ የቆረጥኩባቸው አህቶች ይኖራሉ:: ድንገት ለትዳር ተጠይቀው ፈጽሞ ካላሰብኩት ሰው ጋር ሲጣመሩ ሳይ እንደው የአላህ ነገር ይገርመኝና በጣም አገረሜላሁ:: ይህም የአላህ ሥራ ነው እላለሁ!!:: ሰው አያገኝም ብሎ ወስኖብህ እና ተወራርዶብህ ፒጮር ድንገት የሆነ ነገር ስታገኝ አስቲ አስበው:: ማንም ያልጠበቀው ድንገቴ ሪዝቅ ያልኩት ይህንኑ ነው::

አናስ ... አናማ ወዳጄ ሆይ! ስላልተሣፈልህ ነው እንጂ ስትንከረፈፍ ያመለጠህ አንድም ዕድል የለም:: አንተ ያሰብከው ነገር ለሌላ ሰው ተሠዮቶ ስታይ የኔን ነው የወሰደው ብለህ አታልቅስ:: ያንተ ተቀምጦልሃል፣ በአስፈላጊው ጊዜና ሰዓትም ይሠጥሃል:: ሪዝቁን የወሰደ እንጂ እጅ ጠምዝዞ የሰው የቀማ ሰዉም የለም:: አላህ ለባሮቹ ሁሉ በፍትህ ያድላል። እኔ ብቻ ቀረሁ የኔስ የታለ! ብለህ ብዙ አትጨነቅ:: ሰበቡን ከማድረስ ጋር ዝምብለህ በኢማን፣ በተስፋና በትዕግስት ተራህን ጠብቅ:: መጠበቅ ዒባዳ ነው ብዬህ የለ ባለፈው:: ወሰላም::

ያልፋል፣ ያንሳል፣ ያልቃል ...

- ሊያንዳንዱ ችግር በጊዜ ሂደት ሊያነሰ ይሄዳል፣
- ሊያንዳንዱ ሀሳብ ከዘመን ጋር ያልታል፣
- ቁጭትት ሁሉ እየተሸረሸረ ይመጣል፣
- የማያስፈራንም ሆነ ወደፊት ይከሠታል ብለን የምንሰጋው ነገር ሁሉ ካሰብነው በታች ነው ኢንሻአላህ።
- ዘውታሪ የሆነ ሀመም የለም፣
- የማያልፍ አደጋም አይኖርም ፣
- የዘላለም ችግር አይታሰብም፣
- ለምላካችን ከአቅማችን በላይ መከራ አያሸክመንም፣
- ሁሉ አልፎ ደግ ነገር መምጣቱ አያቀርም፣
- ነገ መልካም ይሆናል ቢሊዝኒላህ።

ሰላም ለኒቃቢስቶች

አኔ መተግበር ያልቻልኩትን ነገር ሌሎች ተግብረው ሳይ ደስስስ ይለኛል። ከኔ በላይ አላህን የሚታዘዙትን ሳይ ፊቱ ይፈካል። ከሁሉ በፊት አላህ እንዲያፀናቸው መለመን ይቀለኛል። ለኔ ኒቃብ ማለት የሸሪዓችንን ፍፁማዊ ፍትህና ጥበብ የማይበት መነጽር ነው። ከኢስላም ዉበቶች መካከልም አንዱ ነው። ሁሉም የቻለዉን ያህል አላህ ባዘዘው ነገር ላይ ይታገስ። የደከምነዉንም ያጠንክረን፣ ይርዳን።

ሰላም ለሙተነቂቦች ...

- ሰላም አላህ ይህን አለባበስ ግዴታ አድርጉብናል ብላችሁ ለምትለብሱ ሁሉ፣
- ሰላም ወደ አምላካችሁ ለመቃረብ ኒቃብን ለምትለብሱ ሁሉ፣
- ሰላም የአላህን ዲዬታ ለማግኘት ደፋ ቀና ለምትሉ ሁሉ፣
- ሰላም ፊትናዎቸን ተቋቁማችሁ በፅናት ለዘለቃችሁ ሁሉ፣
- ሰላም ለመልካም የአላህ ባሮች ሁሉ፣
- አላህ ያጽናችሁ። ሰላማችሁ ይብዛ።

እርምት ስድብ አይደለም ..

ሰዓት ከመድረሱ በፊት ቢሮዬ ጉብቼ ለከላሰ እየተዘጋጀሁ ነው። እዉሰጥ መኖሬን ያላወቁ ተማሪዎቼ በሩ ላይ ቆመው ያወራሉ። በመሃል "ማን ነው የዛሬዉን ከላሰ የሚገባልን?" አለች አንደኛዋ። "ሙሐመድ ነው።" አለቻት ሌላኛዋ። "መሐመድ መላጣው?" አለቻት ተቆብላ። "ማነው ደግሞ መላጣ ያደረገው?" አለቻት ሌላኛዋ ጣልቃ ገብታ። ያች ጂልባብ ለባሿ እንደሆነች በድምጽ ለይቻታለሁ። መከራከር ጀመሩ። ያችኛዋ መላጣ ነው ትላለች፤ ይህችኛዋ ደግሞ መላጣ አይደለም ትላለች። በርግጥ ያችኛዋ ሌላ ሙሐመድም ሰላለ ቃሉን ለምልከት ተጠቀመችው እንጂ ለክፋት አይመስለኝም። ይህችኛዋ ደግሞ "መላጣ" ማለት ጎርብጣት ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ "በተለያዩ ምክንያቶች" መላጣነቴ አልታያት ይሆናል። "ምክንያት" የሚለው ይሰመርበት። ብቻ እኔም ከርከሯን አልወደድኩም። እውነትን መካድ ነዉና። ግትርነቷም ገርሞኛል።

ወደ ነጥቡ ልምጣላችሁ። የዚህ ዓይነቱ አካሄድ ጭፍን ተከታይነት ይባላል። ከመላጣው ርዕሰ ከፍ ብለን ነገሮችን አንመልከት። ሌሎች ጉዳዮችንም እናካትት። አንድን ሰው መገለጫው በሆነው እና ገልጽ ሆኖ በሚታይ ነገር መግለጽ ስድብ ወይም ዉርደት ሊሆን አይችልም። ከብሩን መንካትም አይመስለኝም። እሱን መዳፈርም አይደለም ብዬ አስባለሁ።

ግና ብዙዎቻችን አንድን ሰው በጣም ሰንወድ ወይም ስናከብረው በግልጽ የሚታየው ከፍተቱ ጫምር አይታየንም፤ ጥፋቱም አይገለጥልንም። ጉድለቱን ጭምር እያየን እንከዳለን፣ ጥመቱንም አይተን እንዳላየን እንሆናለን። ለከባባድ ስህተቱ እንኳን የማይመስል ውዝር እንፈልግለታለን። ስለዚያ ሰው አውነታ የተነገረ እንደሆንም እንዴት ተነካብን ብለን እንሞግታለን፣ እንገጣማለን። እንዲህ መሆኑ በርግጥ ሰዉየዉን ቢጎዳው እንጂ አይጠቅመዉም። በስህተቱ እንዲቀጥል ያደርገዋል እንጂ አይመልሰዉም። ያልፈሰፍሰዋል እንጂ አያጠነክረዉም።

እንኩማ ....

አንድን ዓሊም፣ መምህር፣ ዳዒ፣ ኡስታዝ ... ልንወድ ወይም ልናደንቅ እንችላለን። ግና ባጠፋ ጊዜ ጥፋቱን ማሳየት ግድ ይላል። በርሱ የመጣ በዐይኔ የመጣ ብሎ ስህተቱን መሸፋፈን ትክክል አይደለም። ሰዉን አይሳሳትም ብሎ ማሰብ አብሪት ነው፤ጅህልና

ነው፡፡ እኛ ስለወደድነው ብቻ አንድ ሰው ፍፁም በሆነ መልኩ ንፁህ ሊሆን ሊይችልም፤ ፍፁምና የማይሳሳት አንዳልሆነም ልናውቅ ይገባል፡፡

ሰው ሲያጠፋ በይፋም ሆነ በድብቅ የምንናገረው ለማሰተካከል ነው፤ ራሱን እንዲፈትሽ ለማንቃት ነው፤ እንዲታረም ለማስታወስ ነው፡፡ አትናገሩት፤ አትዳፈሩት ማለት ሰዉዬዉንም ኡማዉንም ያበላሻል፡፡ ለሚታይ ጥፋት ያልሆነ ዉዝር መፈለግም አጉል መጃጃል ነው፡፡

ከዚህም አልፈው በሰዉየው ላይ ሸይጧንን የሚያበሩ አሉ፡፡ ጥፋትሀን አትመን፤ ስህተትህን አትቀበል፤ ይቅርታ አትጠይቅ ይሉታል፡፡ ይህ ደግሞ ሰዉዬው አሰተዋይ ካልሆን በስተቀር የበለጠ እንዲታበይ ያደርገዋል፡፡ እውነትን እንዳይቀበል ያግዘዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ብዙ ሰዎች ይሳሳታሉ፡፡ ከሐቅ መንገድ ያፈነግጣሉ፡፡

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በኛ ምልከታ ትሁት እና አላህን የሚፈሩ ሰዎች ሲታረሙ እናያለን፡፡ የደጋፊያቸዉን ብዛት ጥሰው ሐቅን ይናገራሉ፡፡ ተሳስቻለሁ ማለትን አይፈሩም፡፡ ያኔ አጥብቀው የተከራከሩላቸው ሰዎች ግን ያፍራሉ፡፡

እና መውደድና ማከበር ዐይናችሁን እንዳይጋርድ ተጠንቀቁ፡፡ ሰው ሆኖ የማይሳሳት የለም፡፡ ኸሊፋው ዑመርም ተሳስተው እንዲት ሴት መልሳቸው ስህተታቸዉን ተቀብለዋል፡፡ ደጋኞች ሰው ተሳሳተ ማለት ተዋረደ ማለት እንዳልሆነ ያውቃሉ፡፡ ስለሆነም ስህተታቸዉን በደስታ ይቀብላሉ፡፡

ኡስታዞቻችሁን በልከ ዉደዱ፡፡ ዑለሞቻችሁ ላይ በዉዴታ ድንበር አትለፉ፡፡ ሰዎችን የምንከተለው ትክክል እስከሆኑ ብቻ እንደሆነ እወቁ፡፡ የሃሳደንቃቸዉም እውነትን ይዘው እስከፀኑ መሆኑን አትርሱ፡፡ ሲሳሳቱ ኢደብ ባለው መልኩ ሳናዋርድና ሳናስደነግጥ ተሳስታችኋል እንላቸዋለን፡፡

በተረፈ መላጣን መላጣ ነው ማለት ስድብ አይደለምና ዉይ ኡስታዚዚዚዚ ..... እንዴት ይሳሳታል አትበሉ፡፡

በበኩሌ ያች መላጣ "አይደለም" የምትለው አናዳኛለች፡፡ ጭፍን ከሀደትን አልወድም፡፡ እኛ የሰው ልጆች ግን ብዙ ነገሮች ላይ እንደዚህ ነን፡፡ ግትሮችና ደረቆች፡፡ ሐቅን እያወቅን ለራሣችን ከብር ስንል በይሉኝታ የምንሸፋፍን እቡዮች፡፡

አናንተ ሰዎች ነገሮችን በሥማቸው ለመጥራት ስለምን ትፈራላችሁ!!

እያረፍን ...

ወዳጄ ... ችላ የሚልህ ሰው ካለ፣ አትለማመጠው:: ካልፈለገህ አትለምነው፣ ከምንም ካልቆጠረህ አንተም ከሕይወቱ በመውጣት አከብረው:: ጠይቀኸው ከመሰሰ መለስልህ:: ካልሆነ ምን አርጊው ነው ብሎ ብዙ እያሰበ እያሰላሰለ የሚያከመመዉን ንፁህ ቀልብህን ከሱ በመራቅ አሳርፈው:: ቅን እና የዋሁ ቀልብህ አረፍት የሚያስፈልገው ሳለ አላስፈላጊ መስዋእትነት በመክፍል አትጉዳው:: ያለምክንያት የሚጣሉህንና የሚያኮርፉህን እንዳንድ ሰዎችን ማጣት ጤና ነው:: ከሕይወትህ መውጣታቸው ሰላም ነው:: በዚህ ዉሳኔ ላይ በመድረስህ ደግ አረግኩ ብለህ የማትጮቤበት፤ እንኳን! የምትልበት ቀን ይመጣል አብሽር::

****

አትጠራጠሩ ... ሰው በየቀኑ ሊሳሳት ይችላል:: ግና ወደ መጥፎ መንደር ዘው ብሎ ገብቶ ሰው ወዲያው መውጣትን ልማዱ ያደረገ ሰው መቼም ቢሆን ወድቆ አይወድቅም፣ በሂደት ይፀናል፣ ይረጋጋል፣ ቀጥ ይላል::

****

ሰዎች ሆይ! ሰንት ቆሻሻ ካልሲ አለ በምርጥ ጫማ የተሸፈነ::

****

ለመኖር ስትል ጠንካራ መሆን ግድ ይላል:: በርግጥ በዚህ ዘመን በሰዉነትም ጭምር ወፍራም ቆዳ መሆን አለብህ:: ግና ጠንካራ ስልህ በሰዉነት ብቻ አይደለም፣ የሥነልቦና ጥንካሬ፣ የትዕግሥት ጥንካሬ፣ ችግርን የመቻል ጥንካሬ፣ ከሰው ጋር የመኖር ጥንካሬ፣ ከጥሩዉም ከመጥፎዉም አየር ጋር የመኖር ጥንካሬ፡ የዱንያን ጥፍጥናዋንም መራራዋንም የመቀበል ጥንካሬ፣ አላስፈላጊን ነገር የመራቅ እና የመተው ጥንካሬ:: ከሁሉ በላይ ደግሞ የኢማን ጥንካሬ ያስፈልግሃል:: ኢማንህን ካጠነከርክ ኢማን ሊካላከለው የማይችለው መከራ የለም::

****

ወዳጆቼ ... ትልቁ ቅርበት በቤት ጉርብትና አይደለም:: በዝምድናም አይደለም:: በአካልም በቦታም አይደለም:: ትልቁ የሰው ልጅ ቅርበት በኢማን ትስስር ነው፣ ቅርበት በመንፈስ ነው፣ ቅርበት ሀሳብ ለሀሳብ በመግባባት ነው፣ ቅርበት የነፍስ በነፍስ ዉስጥ መግባትና መገኘት ነው:: በአካል ቅርብ ለቅርብ ሆኖ ሩቅ የሆነ በመንፈስ የተሳሳረ ስንት አለ መሠላችሁ! እኛ ጋር ሆኖ የሌለ፣ ሌላ ቦታ ሆኖ እኛ ጋ ያለ፣ እሩቅ ሆኖ ቅርባችን ያደረ ስንት አለ!!

በሰው እጅ መለካት ..

ሚዳቋ ወንዙ ዳር ቆመችና "ጥልቀቱ ምን ያህል ነው?" አለቻት ለተሙኒ::

"ጉልበት ድረስ ቢሆን ነው::" አለቻት::

ዘልላ ገባችበት፣ ወንዙ ሊዉጣት ምንም አልቀረ:: የሞት ሞቷን እንደምንም ተግፍታና ተፍጨርጭራ ወደ ዳር ወጣች::

እያለከለከችና አንገቷን እያወጣች "እንዴ ቅርብ ነው አላልሽኝም እንዴ!" አለቻት::

"አምን እኮ ጉልበቱ ድረስ ቢሆን እኮ ነው::" አለቻት::

በሕይወትህ ጉዳይ እንድን ሰው ሰታማክር ሊመልሰልህ የሚችለው ከሚያውቀው፣ ከኖረው እና ከልምዱ በመነሳት ነው:: መፍትሄዉንም ከራሱ አንፃር ይነግርሃል:: ግን ይህ አሱ የሚነግርህ መፍትሄ ለሱ እንጂ ላንተ ላይጠቅም ይችላል:: ምክንያቱም አንተ አሱ አይደለህማ::

ዱንያ ላይ ስትኖር ያንተ ሕይወት እንደሌሎች ሕይወት አይደለም:: አንዳንድ ገዘ ፍውም የተለያያችሁ ትሆናላችሁ:: ባህሪያችሁ አይመሳሰልም፣ አፈጣጠራችሁም አይቀራረብም፣ ጉዳያችሁም አይገናኝም:: የሚያስደስትህ ላያስደስታቸው፣ የሚያሳስብህ ላያሳስባቸው ይችላል::

ለአንዳንዱ ዱንያ ምንም ናት:: ኑሮዋ ገር ነው:: በሱ እይታ ሥራም፣ ትምህርትም ማኅበራዊ ኑሮም፣ ትዳርም ቀላል ነው:: የሚያስጨንቀው ምንም ነገር የለም:: ሁሉን ነገር ዘና ብሎ ይወጣዋል:: ስለዚህ ቀለል አድርጎም ይነግርሃል:: ታዲያ ስለ ዱንያ ብታማክረው ከዚህ የዘለለ ጉዳይ ላይነግርህ ይችላል:: የኖረዉን እንጂ ያልኖረዉን ከየት ያመጣልሃል!:: ሌላው ደግሞ በተቃራኒው ነው፣ ሁሉን ነገር ያከብዳል፣ ይፈራል፣ ይጨነቃል፣ ይሸሻል::

ሕይወት ግን በሁለቱ መካከል ናት:: ፍፁም በሆነ መልኩ አንድን ሰው ብቻ አትመስልም:: ሕይወት ማለት አንድ ሰው እንዳልሆነች እወቅ:: እንዲሁ አንድ ኪታብ ብቻም አይደለችም:: ስለዚህ ትምህርትም ሆነ ምክርን ከአንድ ወገን ብቻ አትውሰድ:: የአንድን ሰው ብቻ ሀሳብ ወስደህ ከራስ ሕይወት ጋር ለጥፈዋለሁ አትበል፣ ትሳሳታለህና አቋም አትያዝ ይላሉ:: ከቻልክ ሁሉን የተረዳ ሚዛናዊ ሰው ካገኘህ ፊልግና ከሱ ተማር::